ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

# የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት

## መመሪያ ቁጥር 25/2017

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ነሐሴ 2017 ዓ.ም

## መግቢያ

የኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ አቀራረብ፣ ሙግት ማከናወን፣ እና የሪከርድ አሰራር እና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት ዳኞች፣ሬጅስትራሮች እና ሌሎች የሚመለከታቸው የፍርድ ቤቶች ሰራተኞች እንዲሁም ባለጉዳዮች፣ መዛግብትን እና ሰነዶችን በቀላሉ እና በፍጥነት እንዲከታተሉ፣ ጉዳዮችን እንዲፈጽሙ እና እንዲያስፈጽሙ የሚያስችል በመሆኑ፣

ባለጉዳዮች ፍርድ ቤት በአካል መቅረብ ሳይስፈልጋቸው፣ በተፈቀደላቸው የኤሌክትሮኒክ ስርዓቶች በመጠቀም፣ ባሉበት ሆነው በማንኛውም ጊዜ አቤቱታም ሆነ ሌሎች ሰነዶችን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ እና በሙግት ሂደቱም እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው በመሆኑ፣

የሠነዶችን ዝውውር እና ተደራሽነት በሲስተም በመገደብ እና በመቆጣጠር የመዛግብትን መጥፋት፣ መበላሸት፣ መደበቅ እና በእጅ ንክኪ ምክንያት የሚከሰቱ የአሰራር ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚረዳ በመሆኑ፣

የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ውሳኔዎችንም ሆነ ሌሎች የፍርድ ሂደቶችን በቀላሉ ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ ግልፅነትን ለማስፈን የሚረዳ እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ፣

ከአቤቱታ አቀራረብ፣ሙግት ማከናወን እና ሪከርድን ከማስተዳዳር ጋር በተያያዘ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ዘዴ አገልግሎት አሰጣጥ የህግ ተቀባይነት እና ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 50(3) መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### <u>አንቀጽ 1</u>

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ መመሪያ "**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት መመሪያ ቁጥር 25/2017**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ትርጉም**</u>

(1) **"የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት"** ማለት ከዚህ በኋላ **"ስርዓቱ"** ተብሎ የሚጠራ የፍርድ ቤቱ የተቀናጀ የጉዳዮች አስተዳደር የመረጃ ስርዓት (Integrated Case Management Information System) አካል የሆነ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ነው።

(2) **"የተቀናጀ የጉዳዮች አስተዳደር የመረጃ ስርዓት"** (Integrated Case Management Information System) ማለት የኤሌክትሮኒክ ስርዓትን በመጠቀም በፍርድ ቤቶች ውስጥ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ስርዓት ሲሆን በውስጡም የአቤቱታ አቀራርብ፣ የመዝገብ አከፋፈት፣ አያያዝ እና አቀራረብ፣ የቀጠሮ አሰጣጥ፣ የመጥሪያ አደራረስ፣ የባለጉዳዮችና



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ምስክሮች መቅረብና የማስረጃ አቀራረብ፣ የመስማት እና ሙግት፣ እና ሌሎች በችሎት እና በሬጅትራር በኩል የሚከናወኑ ተግባራትን በኤሌክትሮኒክ ስርዓት እና ቴክኖሎጂ ተደግፎ የሚከናወንበትን ስርዓት ያጠቃልላል።

(3) **"የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ"** ማለት በኤሌክትሮኒክ (በኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ) በተደገፈ ዘዴ አቤቱታ፣ ማመልከቻ፣ አባሪ፣ መጥሪያ፣ ቃለ-መሃላ፣ ትእዛዝ፣ ውሳኔ፣ ፍርድ፣ ወይም ማንኛውም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚቀርቡ ሰነዶችን ወደ ፍርድ ቤት የማስገባት ስርዓት ነው።

(4) **"ሙግት ማከናወን"** ማለት በፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚከናወኑ የሙግት ሂደቶችን በሙሉ ማለትም ከአቤቱታዎች እስከ ፍርድ አፈጻጸም ያሉ ተግባራትን በሙሉ ያጠቃለለ ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚኖረውን ሂደት ከጅምር እስከ ፍጻሜ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተደገፈ ዘዴ ማከናወን ሲሆን የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ዘዴ፣ የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና የርቀት መስማትን ያካትታል።

(5) **"ተከራካሪ"** ማለት የፍርድ ሂደት አካል የሆነ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሲሆን በኤሌክትሮኒክ የአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ውስጥ አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከላከል የሚሳተፍ የስርዓቱ ተጠቃሚ ነው። ተከራካሪ ግለሰብ ተከራካሪ ወይም ተቋማዊ ተከራካሪ ሊሆን ይችላል።

(6) **"ግለሰብ ተከራካሪ"** ማለት በፍርድ ቤት ስርዓት ውስጥ ራሱን የሚወክልን ወገን ወይም በግል ጠበቃ አማካይነት ወይም በግል የህግ ተወካዩ አማካይነት የሚሳተፍ ተፈጥሯዊ ሰው ማለት ሲሆን በፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1249/2013 ላይ ጠበቃ የሚል ስያሜ የተሰጣቸውን እና በህግ በተፈቀደው መሰረት በግል ተወክለው ጉዳዮችን የሚያቀርቡ፣ ምላሽ የሚሰጡ፣ ወይም በሌላ በማንኛውም የሙግት ተግባር የሚሰማሩ ግለሰቦችን ያጠቃልላል።

(7) **"ተቋማዊ ተከራካሪ"** ማለት በህግ በተሰጠው ስልጣን፣ ባለው የህግ ሰውነት፣ ወይም ባለው ህጋዊ ፈቃድ እና በተሰጠው የህግ ውክልና መሰረት በፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ የሚሳተፍ የአቃቤ ሕግ ተቋምን፣ የመንግሥት ተቋምን፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትን፣ የንግድ ድርጅትን፣ ወይም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅትን ያካትታል። ተቋማዊ ተከራካሪ በሰርዓቱ ውስጥ ባስመዘገበው ግለሰብ ተከራካሪ ይወከላል።

(8) **"የኤሌክትሮኒክ መዝገብ"** ማለት በኤሌክትሮኒክ መልኩ የተዘጋጀ የፍርድ ቤት መዝገብ ሲሆን በውስጡ ከተከራካሪ ወገኖችም ሆነ ሌሎች ከጉዳዩ ጋራ አግባብነት ያላቸው ወገኖች አቤቱታዎችን፣ ማስረጃዎችን፣ ከፍርድ ቤቱ የተሰጡ መጥሪያዎችን፣ ትእዛዞችን፣ ብይኖችን፣ ፍርዶችን እና ውሳኔዎችን ያካትታል።

(9) **"ኤሌክትሮኒክ ሪከርድ"** ማለት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፍርድ ቤቱ የተቀበለው፣ የተላከለት፣ ግንኙነት ያደረገበት፣ ያዘጋጀው፣ ወይም ያስቀመጠው የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ሪኮርድ ሲሆን ለፍርድ ቤት የቀረቡ አቤቱታዎች፣ ከፍርድ ቤት የመነጩ ሰነዶችን፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተቀመጡ ማስረጃዎች፣ የጉዳይ መዝገብ አካል ተደርጎ የቀረበ ዳታ እንዲሁም የምስክር ቃልና የቃል ክርክር የኤሌክትሮኒክ ድምጽ እና ቪዲዮ ቅጂን ያጠቃልላል።



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

(10) **"የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አስተዳደር ስርዓት"** ማለት የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ዝግጅት፣ ማጠራቀም፣ ተደራሽነት፣ የደህንነት ጥበቃ፣ ቆይታ፣ ማስወገድ እና የመሳሰሉት ሪከርድን ከመምራት ጋር የተገናኙ ተግባራት የሚከናወኑበት የኢንፎርሜሽን ስርዓት ነው፡፡

(11) **"የሪከርድ ባለቤት"** ማለት የአንድ በስርዓት ውስጥ ባለ ሪከርድ ባለቤትነት ያለው ተጠቃሚን የሚመለከት ሆኖ በሪከርድ ውስጥ ያለውን መረጃ ትክክለኛነት እና ሙሉነት የማረጋገጥ፤ ሪከርዱን የማረም፤ የማስተካከል እና የመሠረዝ ፈቃዶችን ጨምሮ በሪከርዱ ላይ ዋና ኃላፊነት እና ቁጥጥር ያለው ማለት ነው፡፡

(12) **"የሪከርድ ያዥ እና ጠባቂ"** ማለት የኤሌክትሮኒክ እና የወረቀት ሪከርዶችን በተደራጀ እና በስርዓት በታገዘ ሁኔታ በአግባቡ የመያዝ እና የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠው ማለት ነው፡፡

(13) **"የሪከርድ ተጠቃሚ"** ማለት የሪከርዶችን ይዘት መመልከት እና ማንበብ የሚችል የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት የተከፈቱ ማንኛውም ሪከርድ ተጠቃሚማለት ነው፡፡

(14) **"ኤሌክትሮኒክ ሠነድ"** ማለት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚተላለፉ ማናቸውም ሠነዶች ማለት ነው፡፡

(15) **"የርቀት መስማት"** ማለት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሙግት ወይም መስማት ለማከናወን በፍርድ ቤት በተዘረጋው ስርዓት መሠረት የሚደረግ የመስማት ወይም የሙግት ስርዓት ሲሆን ዳኞች ካሉበት ሆነው ስርዓቱን በመጠቀም የሚሰጡትን የዳኝነት አገልግሎትም ያካትታል፡፡

(16) **"የአቤቱታ አቀራረብ አገልግሎት ማዕከል"** ማለት በዚህ መመሪያ የተመለከቱ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ የማቅረብ እና የርቀት መስማት እና ሙግት እንዲሁም ማናቸውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ የዳኝነት ስርዓትን ለማገዝ በፍርድ ቤቱ የተወከለ ወይም ሚና የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

(17) **"ኤሌክትሮኒክ ፊርማ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1072/2010 ላይ በተመለከተው መሠረት ከኤሌክትሮኒክ መልእክት ጋር በተያያዘ ፈራሚውን ለመለየትና በመልእክቱ የተካተተው መረጃ በፈራሚው የጸደቀ ወይም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል በኤሌክትሮኒክ መልእክት ላይ የተለጠፈ ወይም ከመልእክቱ ጋር ምክንያታዊ በሆነ አኳኋን የተቆራኘ በኤሌክትሮኒክ መልክ ያለ መረጃ ነው፡፡

(18) **"ዲጂታል ፊርማ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1072/2010 ላይ በተመለከተው መሠረት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ዓይነት ነው፡፡

(ሀ) ከፈራሚው ጋር በልዩ ሁኔታ የተቆራኘ፤

(ለ) የፈራሚውን ማንነት መለየት የሚያስችል፤

(ሐ) በፈራሚው ሙሉ ቁጥጥር ስር ብቻ ባለ ምስጢራዊ ቁልፍ የተፈጠረ እና

(መ) አግባብ ካለው ኤሌክትሮኒክ መልዕክት ጋር የተቆራኘ፤ፊርማው ካረፈ በኋላ በፊርማው እና ፊርማው ባረፈበት ኤሌክትሮኒክ መልዕክት ላይ የተደረገን ማናቸውንም ለውጥ ለመለየት የሚያስችል፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

(19) **"ፍርድ ቤት"** ማለት እንደ አግባብነቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡

(20) **"ዋና ሬጅስትራር"** ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር ማለት ነው፡፡

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ ለሴት ጾታም ያገለግላል፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

(1) ይህ መመሪያ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

(2) መመሪያው በክልል ፍርድ ቤቶች አማካኝነት በውክልና በሚታዩ የፌዴራል ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ፍርድ ቤቶቹ ይህን ቴክኖሎጂ ለመተግበር የሚያስችል መሠረተ ልማት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**4. የአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት መርሆዎች**

(1) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ መልክ ለፍርድ ቤት የቀረቡ ሰነዶች ወይም በስርዓቱ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተያዙ ሰነዶች በፍርድ ቤቱ በወረቀት ከተያዙ ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተቀባይነት እና ውጤት ይኖራቸዋል፡፡

(2) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ መልክ በፍርድ ቤት የሚከናወኑ የርቀት መስማት እና ክርክሮች በፍርድ ቤቱ በአካል በመቅረብ ከሚደረጉ መስማት እና ክርክሮች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተቀባይነት እና ውጤት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ስርዓቱ ተጠቃሚዎች

**5. ግለሰብ ተከራካሪዎች**

(1) የስርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰብ ተከራካሪዎች በብሔራዊ መታወቂያ (ፋይዳ) መለያ ቁጥራቸው እና ለፋይዳ ባስመዘገቡት የሞባይል ስልክ ቁጥር በሚላክላቸው የአንድ ጊዜ የይለፍ ቃል አማካኝነት ብቻ ወደ ስርዓቱ መግባት እና መጠቀም ይችላሉ፡፡

(2) ግለሰብ ተከራካሪው ጠበቃ ከሆነ ወደ ስርዓቱ ለመግባት ከፋይዳ መለያ ቁጥሩ እና የአንድ ጊዜ የይለፍ ቃል በተጨማሪ የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ ቁጥሩን ማስገባት አለበት፡፡

(3) ግለሰብ ተከራካሪው ጠበቃ ከሆነ ወደ ስርዓቱ ለመግባት ባስገባው የአንድ ጊዜ መግቢያ የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ደንበኞቹን አቤቱታ ማቅረብ፣ መከታተል፣ እና በሙግት ሂደት መሳተፍ ይችላል፡፡

(4) ግለሰብ ተከራካሪዎች በስርዓቱ ለመጠቀም ምዝገባ ማከናወን አያስፈልጋቸውም፡፡

**6. ተቋማዊ ተከራካሪዎች**

(1) ማንኛውም ተቋማዊ ተከራካሪ በስርዓቱ ለመጠቀም እንዲችል ተቋሙን እና ተቋሙን ወክለው የሚከራከር(ሩ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ ግለሰብ ተከራካሪዎችን በሚኖሩበት ጊዜ ለዚህ ዓላማ የተሰጠው የይለፍ ቃል በአግባቡ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት ለዋና ሬጅስትራር አቅርቦ ማስመዝገብ አለበት፡፡

(2) ማንኛውንም ተቋማዊ ተከራካሪ ወክሎ የሚከራከር ግለሰብ ተከራካሪ ወደ ስርዓቱ ለመግባት የሚወክለውን ተቋም መምረጥ፣ እና የብሔራዊ መታወቂያ (ፋይዳ) መለያውን እና በሞባይል ስልክ ቁጥሩ የተላከለትን የአንድ ጊዜ የይለፍ ቃል ማስገባት አለበት፡፡

(3) ተቋማዊ ተከራካሪን ወክሎ የሚከራከር ማንኛውም ግለሰብ ተከራካሪ በስርዓቱ ውስጥ በተወከለበት(ባቸው) ጉዳይ(ዮች) ላይ ብቻ አቤቱታ ማቅረብ እና ሙግት ማከናወን ይችላል፡፡

(4) ማንኛውም ተቋማዊ ተከራካሪ ተቋሙን ወክለው እንዲከራከር ውክልና የሰጠው ግለሰብ ተከራካሪ ከተቋሙ የተሰጠው ውክልና ሲያበቃ ወይም ሲቋረጥ ለዚሁ አገልግሎት በጠቅላይ ፍርድ ቤት በተዘጋጀው ፎርም ሞልቶ እና ለዋና ሬጅስትራር አቅርቦ ተወካዩ በስርዓቱ ውስጥ ያለው ምዝገባ እንዲሰረዝለትና ተቋሙን ወክሎ በስርዓቱ መገልገሉ እንዲቋረጥ ማድረግ አለበት፡፡

(5) ማንኛውም ተቋማዊ ተከራካሪ ከላይ በተራ ቁጥር 5(4) የተመለከተውን እስከፈጸመበት ጊዜ ድረስ በተቋሙ የተወከለ ግለሰብ ተከራካሪ ውክልናው እንዳላበቃ ወይም እንዳልተቋረጠ ይቆጠራል፡፡

7. <u>የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አጠቃቀም ደህንነት</u>

(1) ማንኛውም ተከራካሪ የፋይዳ መለያ ቁጥሩን እና ለፋይዳ ባስመዘገበው የሞባይል ስልክ ቁጥር የሚላክለትን የአንድ ጊዜ የይለፍ ቃል ተጠቅሞ ሌላ ሰው ወደ ስርዓቱ እንዳይገባ ማንኛውንም ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

(2) የፋይዳ መለያ ቁጥሩን እና ለፋይዳ ባስመዘገበው የሞባይል ስልክ ቁጥር የተላከለትን የአንድ ጊዜ የይለፍ ቃል ተጠቅሞ ሌላ ተጠቃሚ ወደ ስርዓቱ እንዲገባ የፈቀደ ተከራካሪ በስርዓቱ ውስጥ በርሱ መለያ የተከናወኑ ተግባራት በሙሉ በግለሰብ ተከራካሪው በራሱ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

(3) ማንኛውም ተከራካሪ የፋይዳ ቁጥሩ እና ለፋይዳ ያስመዘገበው የሞባይል ስልክ ቁጥር ለሌሎች አገልግሎት ተጋልጧል ብሎ ካመነ ይህንኑ ወዲያውኑ በስልክ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የጥሪ ማዕከል ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር ጽሕፈት ቤት በኢሜይል ወይም በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፡፡ የዋና ሬጅስትራር ጽሕፈት ቤቱ ማሳወቂያው እንደደረሰው በአፋጣኝ የተጠቃሚው መግቢያ ላይ አስፈላጊ የሆኑ የደህንነት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ኤሌክትሮኒክ ሠነድ

### 8. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሠነዶችን ስለማቅረብ

(1) ፍርድ ቤቱ ማናቸውም ሠነዶች በኤሌክትሮኒክ ዘዴእንዲቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

(2) ተከራካሪው በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተጠቅሞ ሰነዶችን ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

(3) ፍርድ ቤት ሠነዶችን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሲቀበል ሠነዱን ለላከው ተከራካሪ ሠነድ መቀበሉን የሚገልፅ የፅሑፍ መልዕክት ማረጋገጫ ይልካል። ይህ የሰነድ መቀበል ማረጋገጫ በተላከበት እለት ሠነዱን ለላከው ሰው እንደደረሰው ይቆጠራል።

(4) የሚመለከተው ፍርድ ቤት የኤሌክትሮኒክ ሰነዱን የተቀበለበት ቀን አቤቱታው ወይም ሰነዱ ለፍርድ ቤቱ የደረሰበት ቀን ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም ሰነዱ በፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ ስርዓት ውስጥ የሚገባበት ቀን ሰነዱ በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የሚደረገውን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫን ሲያጠናቅቅ ነው።

(5) ፍርድ ቤቱ ለግለሰብ ተከራካሪው የላከውን የሠነድ መቀበያ ማረጋገጫ በማስረጃነት መያዝ አለበት።

(6) ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ መሆኑን ባመነ ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች የኤሌክትሮኒክ ሠነድ ዋናውን ቅጂ እንዲያቀርቡ ሊያዝ ይችላል።

(7) ተከራካሪ ወገኖች የአቤቱታ አቀራረብ ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት በፍርድ ቤቱ የአገልግሎት ማዕከላት መገልገል ይችላሉ።

**9. <u>የኤሌክትሮኒክ ሠነዶች አቀባበል ሁኔታዎች</u>**

(1) የኤሌክትሮኒክ ሠነዶች በሚከተለው ዘዴ ለፍርድ ቤት ይቀርባሉ፤

ሀ) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ አማካኝነት ሰነዱን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በማስገባት፣

ለ) ጉዳዩ ለቀረበለት ፍርድ ቤት የወረቀት ሰነድ በቀረበ ጊዜ የወረቀት ሰነዱን ስካን (scan) አድርጎ ወደ ኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ በማስገባት፣

ሐ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሎች እና በክልል ፍርድ ቤቶች ውስጥ በሚያደራጃቸው የአገልግሎት ማዕከላት በመገልገል ሰነዱን በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በማስገባት፣

(2) ከላይ በቁጥር 9(1) ስር በተገለፀው አግባብ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ኤሌክትሮኒክ ሠነዶች ከዚህ መመሪያ አባሪ የተደረጉ የፍርድ ቤቱን ፎርማት እና በህግ የተመለከቱ ፎርሞችን የተከተሉ፤ የመዝገብ ቁጥር እና ስም ያላቸው፤ ስለ ተያያዘው ሠነድ ዝርዝር ሁኔታ የሚገልፅ መግለጫ የያዙ መሆን አለባቸው።

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 9(1) ስር የተመለከተው ቢኖርም በዳኛ በተለይ ካልተፈቀደ በስተቀር የሚከተሉት ሠነዶች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይችሉም።

ሀ) በዝግ ችሎት የሚታዩ ጉዳዮች ሰነዶች

ለ) በህግ ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ምስጢራዊ የተባሉ ሰነዶች

ሐ) በምስጢር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው አቤቱታ ወይም በስር ፍርድ ቤት ባለው መዝገብ በሚስጥር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው አቤቱታ፤

ሠ) በሚስጢር እንዲጠበቅ ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት ሃሳብ የቀረበበት አቤቱታ፤

(4) በሚስጥር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው ማንኛውም አቤቱታ፣ ምስጢር የሆነው ጉዳይ በቀለም እንዲሸፈን (redact) የተደረገበት ሰነድ ያለው አቤቱታን ጨምሮ፣ ለፍርድ ቤት

የሚቀርበውም ሆነ ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ የሚደረገው በስርዓቱ አማካኝነት ሳይሆን በወረቀት በቀረበ አቤቱታ አማካኝነት ነው፡፡

10. **<u>በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሰነድ ስለመቅረቡ ማስረጃ</u>**

በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት ለተከራካሪ የተላከ የኤሌክትሮኒክ ማረጋገጫ ሰነዱ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለመቅረቡ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡

11. **<u>በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት በቀረቡ ሰነዶች ላይ ስለመፈረም</u>**

(1) የኤሌክትሮኒክ ፊርማ በእጅ ከተፈረመ ዋና ፊርማ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተፈጻሚነት እና ውጤት ይኖረዋል፡፡

(2) በበቂ ምክንያት ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር፣ በኤሌክትሮኒክ የተፈረመ ሰነድ ወደ ስርዓቱ ከገባ በኋላ፣ በማንኛውም ሁኔታ አይሰረዝም ወይም አይለወጥም፡፡

(3) በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ ተከራካሪ የሚያቀርበው አቤቱታ የተከራካሪውን የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የሚያካትት ሲሆን በዚህ ሁኔታ የቀረበ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ) የተከራካሪው ፊርማ በሚያርፍበት ቦታ ላይ "/s/" ከሚል ምልክት ጋር የተጠቃሚው ሙሉ ስም፣ ወይም

ለ) ስካን (scan) የተደረገ የተከራካሪው ፊርማ ወይም በይፋዊ ቁልፍ (public key) የተዘጋጀ ኤሌክትሮኒክ ፊርማ

(4) ሰነዱ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ የተረጋገጠ ከሆነ ወይም በህግ በተፈቀደለት ሰው ፊት በቃለ-መሃላ የተረጋገጠ ከሆነ፣ የተከራካሪው ዋና ፊርማውን(ዎችን) ባከተተ መልኩ ሰነዱን ስካን (scan) አድርጎ በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ ዘዴ ማቅረብ አለበት፡፡

(5) ሰነዱ የተቃራኒ ወገን ፊርማን የሚጠይቅ ከሆነ፣ ተከራካሪው ሰነዱን በኤሌክትሮኒክ የአቤቱታ አቀራረብ ዘዴ የሚያቀርበው የተቃራኒ ወገን ፊርማ ሰነዱ ላይ ከሰፈረ በኋላ ሠነዱን ስካን (Scan) አድርጎ ወደ ስርዓቱ በመጫን ነው፡፡

(6) ከላይ በአንቀጽ 11(1-5) የተገለፀው የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ቢኖርም አስፈላጊው መሠረተ ልማት እና የህግ ማዕቀፍ ሲኖር ፍርድ ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ፊርማ በአስገዳጅነት እንዲተገበር ሊያደርግ ይችላል፡፡

12. **<u>ሰርቲፊኬት ሰጪ</u>**

በፍርድ ቤቱ አገልግሎት ላይ በዋለው በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የኤሌክትሮኒክ ሰነዶች ላይ ኤሌክትሮኒክ ፊርማቸውን ለሚፈርሙ ዳኞች፣ ሬጅስትራሮች፣ ጠበቆች፣ አቃቢያነ ህግ፣ ፖሊስ፣ እና የማረሚያ ቤት ኦፊሰሮች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር 1072/2010 መሰረት የኤሌክትሮኒክ ሰርቲፊኬት፣ የምስጠራ እና የጊዜ ማህተም አገልግሎት ይሰጣል፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## 13. <u>በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት አማካኝነት የሚቀርቡ ቃለ-መኃላዎች፣</u>

(1) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት ለፍርድ ቤት የቀረበ ቃለ-መሃላ በፍርድ ሂደቶች ሁሉ በወረቀት ከቀረበ ቃለ-መሃላ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ለተመሳሳይ ዓላማ በፍርድ ቤቶች ውስጥ በአገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

(2) በስርዓቱ ተጠቅሞ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ቃለ-መሃላ በፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 206 ላይ በተደነገገው መሰረት በማንኛውም ፍርድ ቤት ወይም ዳኛ ፊት ወይም ስልጣን ያለው አካል ፊት ወይም ፍርድ ቤቱ መርጦ ይህን ሥነ ሥርዓት እንዲያስፈጽም ባዘዘው ሰው ፊት የተፈጸመ ቃለ-መሃላ መሆን አለበት፡፡

(3) በስርዓቱ አማካኝነት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ቃለ-መሃላ በህጉ መሰረት በወረቀት ላይ ተዘጋጅቶ የተፈረመው ቃለ-መሃለ ትክክለኛ እና የተሟላ የኤሌክትሮኒክ ቅጂ ስካን (scan) ተደርጎ የተዘጋጀ መሆን አለበት፣

(4) ቃለመሃላው በጠበቃ የቀረበ እንደሆነ ከጉዳዩ ጋር የሚቀርብ ቃለ-መሃላ በተከራካሪው የኤሌክትሮኒክ ፊርማ የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

(5) ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን አንቀጾች መሰረት የሚቀርብ ቃለመኃላ በዚህ መመሪያ አባሪ 6 ስር በተመለከተው አግባብ መቅረብ አለበት፡፡

## 14. <u>በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ እና ሠነድ ማቅረቢያ ጊዜ አቆጣጠር</u>

(1) ተከራካሪ በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ተጠቅሞ በማንኛውም ቀን የበዓል እና የእረፍት ጊዜያትን ጨምሮ በማንኛውም ሰዓት ሰነዶች ለፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል፡፡

(2) ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ለመድረስ የጊዜ ገደብ ያለበት ሰነድ በጊዜው ቀርቧል ተብሎ የሚወሰደው የሰነዱ ማቅረቢያ ቀን ከሚጠናቀቅበት ቀን እኩለ ሌሊት በፊት በስርዓቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ከደረሰ እና ስለመድረሱ በስርዓቱ የተሰጠ መከታተያ ቁጥር ለተጠቃሚው ከደረሰ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በጊዜው የደረሰ አቤቱታ ወይም ሰነድ ለፍርድ ቤቱ የደረሰበት ቀንና ሰዓት በስርዓቱ ተመዝግቦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ይደረጋል፡፡

(3) የሚመለከተው ፍርድ ቤት የኤሌክትሮኒክ አቤቱታውን ወይም ሰነዱን የተቀበለበት ቀን አቤቱታው ወይም ሰነዱ ለፍርድ ቤቱ የደረሰበት ቀን ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሆኖም ሰነዱ በፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ስርዓት ውስጥ የሚገባበት ቀን ሰነዱ በፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር የሚደረገውን የብቃት ማረጋገጫን ሲያጠናቅቅ ወይም መዝገቡ ሲከፈት ነው፡፡ በቀረበው አቤቱታ መሰረት አዲስ መዝገብ የሚከፈት ከሆነ ሰነዱ በፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ስርዓት ውስጥ  የሚገባበት ቀን መዝገቡ ሲከፈት ይሆናል፡፡

## 15. <u>በኤሌክትሮኒክ የአቤቱታ አቀራረብ ዘዴ የቀረበ ሰነድን መገምገም እና መቀበል</u>

(1) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ፍርድ ቤት  የቀረበ ሰነድ መዝገብ የሚከፈትለት በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ቴክኒካል ብቃቱ ተገምግሞ  ተቀባይነት ካገኘ እና (በደሃ ደንብ የሚከፈት መዝገብ ካልሆነ በስተቀር) የዳኝነት ክፍያ ከተከፈለበት ነው፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

(2) በእያንዳንዱ የተከፈተ መዝገብ ሰነድ ላይ የፍርድ ቤቱ ስም፣ የመዝገቡ ቁጥር፣ ሰነዱ የተያያዘበት ቀን እና ሰዓት፣ እና በመዝገቡ ውስጥ ለሰነዱ የተሰጠው ተከታታይ ገጽ ቁጥርን የያዘ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ምልክት በስርዓቱ አማካኝነት በሬጅስትራሩ ይደረግበታል፡፡

(3) የቀረበን ሰነድ ሬጅስትራሩ የቴክኒክ ብቃት ከገመገመ በኋላ ውጤቱን ሰነዱን ላቀረበው ተከራካሪ በስርዓቱ ውስጥ ባለው የተከራካሪው ድረገጽ ክፍል በኩል እና ባለጉዳዩ መዝገብ ሲከፍት ባስመዘገበው ስልክ ቁጥር አማካኝነት አጭር የጽሁፍ መልእክት ማሳወቂያ ይልካል፡፡ በውጤቱ ተቀባይነት ካገኘ እና ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተያይዞ በተከራካሪው የደሃ ደንብ ማመልከቻ ቀርቦ ካልሆነ በቀር መጠኑ የተገለጸ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ሬጅስትራሩ በማሳወቂያ ላይ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በውጤቱ ውድቅ የተደረገ ከሆነ ሰነዱ ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት ሬጅስትራሩ በማሳወቂያው መግለጽ አለበት፡፡

(4) ሰነዱ በሬጅስትራር ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ሰነዱ ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት ካልተቀበለው የሰነዱ ቴክኒካል ብቃት በዳኛ እንዲታይለት በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ አማካኝነት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 16. ምስጢር የሚጠበቅ ጉዳይ ያለው ሰነድ

(1) በምስጢር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው ወይም በበታች ፍርድ ቤት ባለው መዝገብ በሚስጥር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው ወይም በሚስጢር እንዲጠበቅ ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት ሃሳብ የቀረበበት አቤቱታ በስርዓቱ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መቅረብ የለበትም፡፡

(2) በሚስጥር የሚጠበቅ ሰነድ ያለው ማንኛውም አቤቱታ፣ ምስጢር የሆነው ጉዳይ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በቀለም እንዲሸፈን (redact) የተደረገበት ሰነድ ያለው አቤቱታን ጨምሮ፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውም ሆነ ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ የሚደረገው በወረቀት በቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

(3) ሆኖም ምስጢራዊ ሰነድ በስርዓቱ ውስጥ እንዲያዝ አስፈላጊ ከሆነ በስርዓቱ ውስጥ ሊገባ የሚችለው ሰነዱ በስርዓቱ አማካኝነት ከተመሰጠረ (encrypt) ከተደረገ በኋላ ነው፡፡ ሰነዱ የተመሰጠረበት እና የሚፈታበት (decryption) ቁልፍ ጉዳዩን በሚዳኘው(ኙት) ዳኛ(ዳኞች) እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

## 17. ሰነድን ለተቀባዩ ስለማድረስ

(1) የፍርድ ቤት ማስታወቂያ፣ትእዛዝ፣ብይን፣ውሳኔ፣ፍርድ ወይም ማንኛውንም ሰነድ ለተከራካሪው እንዲደርስ የሚደረገው በስርዓቱ ድረገጽ የተከራካሪው ክፍል ላይ በማሳየት፣ ወይም ተከራካሪው ባስመዘገበው የሞባይል ስልክ በአጭር የጽሁፍ መልእክት፣ ወይም በኢሜል ለተከራካሪው እንዲደርስ በማድረግ ነው፡፡

(2) በስርዓቱ አማካኝነት የሚላክ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ መጥሪያ፣ የእስር ማዘዣ ወይም ማናቸውም ተያያዥነት ያለው ሰነድ ስለመላኩ በስርዓቱ ውስጥ በተመዘገበበት ቀን ለተቀባዩ እንደደረሰ ይቆጠራል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

(3) በስርዓቱ አማካኝነት ሰነድ የተቀበለ ተከራካሪ ወገን፣ ሰነዱን ለማንበብም ሆነ ለማውረድ ያልቻለ እንደሆነ ወዲያውኑ ሰነዱን ለፍርድ ቤቱ ያሳውቃል፣ ፍርድ ቤቱም ሰነዱ ለማንበብ ወይም ለማውረድ እንዲቻል ሆኖ እንዲስተካከል አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

18. **ሰነድ ለተቀባዩ ስለመድረሱ ማረጋገጫ**

(1) በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓቱ አማኝነት ለተከራካሪ ወገን የተላኩ ሰነዶች በሙሉ በትክክል እንደደረሰው ተቀባዩ ማረጋገጥ እንዲችል የሰነዶቹን ዝርዝር የያዘ አንድ ሰነድ በመጨረሻ ተካቶ ከተላኩት ሰነዶች ጋር አብሮ በስርዓቱ አማካኝነት መላክ አለበት፡፡

(2) በስርዓቱ አማካኝነት ማንኛውም ሰነድ ለተከራካሪ ወገን ሲላክ እና በስርዓቱ ውስጥ ባለው የተቀባዩ ድረገጽ ክፍል ሲደርስ ስርዓቱ በራሱ ሰነዱ ለተቀባዩ መድረሱን የሚያረጋግጥ ማሳወቂያ በስርዓቱ ውስጥ ለሚገኘው የላኪው ድረገጽ ክፍል እና በተቀባዩ የሞባይል ስልክ በአጭር የስልክ የጽሁፍ መልእክት ይልካል፡፡

(3) ሰነዱ መድረስ አለመድረሱን በተመለከተ አለመግባባት ቢፈጠር፣ ጉዳዩን በመመልከት ላይ ላለው ችሎት ቀርቦ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

19. **በስርዓቱ አማካኝነት በቀረበ አቤቱታ ላይ ለውጥ ስለማድረግ**

(1) በስርዓቱ አማካኝነት ማንኛውም ሰነድ ከቀረበ በኂላ አቅራቢው ሰነዱን ከስርዓቱ ለማውጣትም (withdraw) ሆነ ለመለወጥ አይችልም፡፡

(2) ከላይ በንዑስ ቁጥር (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አቅራቢው ያቀረበውን ሰነድ ማውጣት ወይም መለወጥ ያለበት በሚሆንበት ጊዜ ሰነዱ ለቀረበለት ፍርድ ቤት ሬጅስትራር ማመልከቻ አቅርቦ አስተዳደራዊ መፍትሔ ወይም ጉዳዩን ለሚመለከተው ችሎት ማመልከቻ አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ርቀት መስማት /Remote Hearing/

20. **የርቀትመስማት የችሎት ስነ ስርዓት**

(1) የርቀት መስማት ተሳታፊዎች በአካል ችሎት መቅረብ የሚጠይቀውን ስነ ስርዓት ማክበር አለባቸው፡፡

(2) ተሳታፊዎች በሥነ ምግባራቸው፣ በአነጋገራቸው እና በአለባበሳቸው ለችሎት ሂደቱ ያላቸውን ክብር ማሳየት አለባቸው፡፡ ተሳታፊዎች ይህን ስርዓት በጣሱ ጊዜ አግባብነት ያላቸው የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

(3) በህግ ክልከላ ከሌለ በስተቀር የርቀት መስማት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለሕዝብ ግልፅ ሊደረግ ይችላል፡፡

(4) ስርዓቱ የሚያስተናግደውን ታዳሚ ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት የታዳሚ ቁጥር የሚወሰን ከሆነ የችሎቱ ታዳሚ መሆን ለሚፈልጉ እንደየታዳሚው ጥያቄ ቅደም ተከተል በሬጅስትራር በኩል የይለፍ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

21. **<u>የክርክር አማራጮች</u>**

(1) ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን በችሎት ወይ በርቀት ሆነው ለማከናወን በኤክትሮኒክ ዘዴ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

(2) ተከራካሪ ወገኖች በርቀት መስማት ለመከራከር ሲያመለክቱ እና ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው ችሎት ሲፈቅድ፣ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በአምስት የስራ ቀናት የሚከተሉትን መረጃዎች ዝርዝር መረጃ ለተከራካሪዎቹ እና ለችሎቱ መላክ አለበት፡፡

ሀ) የመዝገብ ቁጥር፣

ለ) የፍርድ ቤቱን ወይም የምድብ ችሎቱን ስም እና አድራሻ፣

ሐ) ጉዳዩ የሚታይበትን ችሎት፣

መ) የርቀት መስማት የሚከናወንበትን ቀንና ሰዓት፣

ሠ) የርቀት መስማት የሚከናወንበትን ድረገጽ አድራሻ ሊንክ፣

ረ) የርቀት መስማቱ እንዲከናወን የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርግ በፍርድ ቤት የተመደበውን ባለሙያ ሙሉ ስም እና ሞባይል ስልክ ቁጥር

(3) የርቀት መስማት ስርዓቱ የሚደረገው በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚቋቋመው የአገልግሎት ማዕከል ከሆነ የተከራካሪው ማንነት በማዕከሉ በሚገኝ አካል ተረጋግጦ ያለ ምዝገባ መሰማቱ የሚከናወን ይሆናል፡፡

22. **<u>ፍላጎትን ስለመጠየቅ</u>**

(1) አንደኛው ተከራካሪ ወገን በርቀት ችሎት ለመከራከር ሲያመለክት ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በርቀት መስማት ለመከራከር ፍላጎት ያለው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የፍላጎት መጠየቂያ ፎርም እንዲሞላ ይደረጋል፡፡

(2) አንዱ ተከራካሪ ወገን በርቀት መስማትን መርጦ ሌላኛው ወገን በችሎት በአካል ቀርቦ መዳኘት ሲፈልግ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ሌላኛው ወገን በርቀት መስማት ችሎት እንዲቀርብ ወይም በችሎት በአካል እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የርቀት መስማቱን የሚያከናውነው ችሎት አንድን ጉዳይ በርቀት መስማት የተሻለ ነው ብሎ ካመነ ጉዳዩ በርቀት እንዲሰማ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

23. **<u>የርቀት መስማት ስለሚደረግበት ሁኔታ</u>**

(1) የርቀት መስማት ለማከናወን ተከራካሪ ወገኖች ወይም ምስክሮች የቴክኖሎጂው ሁኔታ እስከፈቀደ ድረስ በየትኛውም ቦታ ሆነው መከራከር ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን ተከራካሪው ለርቀት መስማት የሚገኝበት ቦታ በቂ የሆነ የመብራት እና የቴሌኮም አገልግሎት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የርቀት መስማት ለማከናወን ተከራካሪ ወገኖች ወይም ምስክሮች በአንድ በፍርድ ቤቱ በተለየ የአገልግሎት ማዕከል ወይም ክርክሩ እንዲከናወን በተመረጠ ተቋም ቢሮ ውስጥ ሆነው መሰማቱ እንዲከናወን ሊያዝ ይችላል፡፡

(3) የርቀት መስማት ድምፅ እና ምስል ቀጥታ (ሪል ታይም) መሆን አለበት፡፡

(4) የርቀት መስማት ምስል እና ድምፅ ለፍርድ ቤቱ አገልግሎት ዓላማ እንዲቀረፅ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ከፍርድ ቤቱ በቀር ማናቸውም አካል የርቀት መስማትን ምስል፤ ሠነዶች እና ድምፅ መቅረፅ፤ መተንተን ወይም ማተም፤ መጠቀም እና ማሰራጨት አይችልም፡፡

(5) በፖሊስ ቁጥጥር ስር ወይም በማረሚያ ቤት ለሚገኝ ተጠርጣሪ ወይም ተከሣሽ የሚመለከተው የፖሊስ ወይም ማረሚያ ቤት አስተዳዳር ለርቀት መስማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት አለበት፡፡

(6) የርቀት መስማት ቀጠሮ ቀን መቅረብ ያልቻለ ወገን ሳይቀርብ የቀረበትን ምክንያት በመግለፅ ለችሎቱ በአሌክትሮኒክ መንገድ አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት በስነ ስርዓት ህጉ ላይ የተመለከተውን አሰራር በመከተል ድጋሚ ቀጠሮ ሊሰጥ ወይም አቤቱታውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 24. <u>ስለ ይግባኝ እና ሰበር መስማት</u>

በርቀት መስማት በተደረገ ክርክር በተሰጠ ውሳኔ ላይ በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ የይግባኝ ቅሬታ ወይም የሰበር አቤቱታ መስማት እንደ ቅሬታ አቅራቢው ምርጫ በተመሳሳይ መንገድ በርቀት መስማት ወይም በአካል በችሎት በመቅረብ ሊከናወን ይችላል፡፡

## 25. <u>የፍትሐብሔር ፍርድ አፈጻጸም ጉዳዮች</u>

(1) የፍርድ አፈጻጸም ሂደት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊፈፀም ይችላል፡፡

(2) በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የአፈጻጸም አቤቱታ የቀረበለት ችሎትም በስርዓቱ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ጽ/ቤት የሆነ እንደሆነ የሃራጅ ሂደት ማለትም በሀራጅ ለመሳተፍ የሚከፈል 25 ከመቶ ክፍያ ፣ ከሀራጅ ሽያጭ በኋላ ለፍርድ ባለመብት ጨምሮ ለተለያዩ አካላት የሚከፈል ክፍያ ፣የሀራጅ መነሻ ግምት እንዲሁም በርቀት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚደረግ የሀራጅ ሽያጭ እና ሌሎች የአፈጻጸም ተግባራት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚከናወን ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## ክፍል አምስት

<u>ስለ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አያያዝ እናአስተዳደር</u>

**26. የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ የህግ ተቀባይነት**

በዚህ መመሪያ መሰረት የቀረበ እና የሚተዳደር የፍርድ ቤት የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ በአዋጅ ቁጥር 1205/2012 አንቀጽ 13 (1) መሠረት የህግ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**27. የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ**

በእያንዳንዱ በፍርድ ቤት ውስጥ ባለ የኤሌክትሮኒክ የጉዳይ መዝገብ ውስጥ የሚከተሉት የፍርድ ቤት የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች ወይም ቅጂዎች ይኖራሉ፤

ሀ) ጉዳዩን በተመለከተ በተከራካሪ ወገኖች፤ በሶስተኛ ወገኖች፣ ወይም በሌሎች አካላት በወረቀት ወይም በጽሁፍ የቀረቡ ሰነዶች፤

ለ) የጉዳዩ መዝገብ ውስጥ በዳኛው የተያያዙ በወረቀት ወይም በጽሁፍ ላይ ያሉ ሰነዶች፤

ሐ) ከጉዳዩ መዝገብ ጋር የተያያዘ ቪዲዮ (ካለ)፣

መ) ከጉዳዩ መዝገብ ጋር የተያያዘ የድምጽ ቅጂ(ካለ)፡፡

**28. የሪከርድ ባለቤቶች፤ ተጠቃሚዎች እና ጠባቂዎች**

(1) የሪከርድ ባለቤቶችሪከርዶችን ሊያነቡ፣ አዲስ ሪከርድ ሊጨምሩ፣ እንዲሁም በስነስርዓት እና በሌሎች ህጎች በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ሊለውጡ፣ ሊያስተካክሉ፣ ሊሰርዙ፣ ወይም ሊያጠፉ ወይም ከነዚህ ተግባራት አንዱ ወይም በርካታዎቹ በሌሎች እንዲፈጸም ስልጣን የሚሰጥ ትእዛዝ ሊሰጡ የሚችሉ ሆነው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

(2) ዳኞች በተመደበላቸው መዝገብ ውስጥ ያሉ ማናቸውም ለፍርድ ቤቱ የቀረቡም ሆኑ ከፍርድ ቤቱ የወጡ የጉዳይ ሪኮርዶች ባለቤቶች ሲሆኑ የፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች እና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በህግ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት የጉዳይ ሪከርዶች እና የአስተዳደር ሪከርዶች ባለቤት ይሆናሉ፡፡

(3) የሪከርድ ያዥ እና ጠባቂዎች በሪከርድ ባለቤቶች ታዘው ካልሆነ በስተቀር ሪከርድ ላይ አዲስ ሪከርድ የመጨመርም ሆነ ሪከርድ የመለወጥ፣ የማስተካከል፣ የመሰረዝ፣ ወይም የማጥፋት ስልጣን ሳይኖራቸው የሪከርድ አስተዳደር ስርዓትን በአግባቡ ለመምራት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፤

ሀ) ሪከርድ ያዥ እና ጠባቂዎች በሚሰሩበት ፍርድ ቤት ውስጥ ያሉ የኤሌክትሮኒክ እና የወረቀት ሪከርዶችን በተደራጀ እና በስርዓት በታገዘ ሁኔታ በአግባቡ የመያዝ እና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ለ) ሬጅስትራሮች፣ረዳት ዳኞች፣ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ ኃላፊዎች፣ ችሎት ፀሃፊዎች እና በስነስርዓት ህጉ መሰረት የሬጂስትራር ተግባራት እንዲያከናውን በሬጂስትራር የተመደቡ፣ ከዳኝነት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ለፍርድ ቤቱ የቀረቡም ሆኑ ከፍርድ ቤቱ የወጡ ሪኮርዶች ያዥ እና ጠባቂዎች ናቸው፡፡

(4) የሪከርድ ተጠቃሚዎች ሪከርዶችን ይዘት ሊመለከቱ እና ሊያነቡ የሚችሉ የሚከተሉት አካላት ናቸው፡-

ሀ) ፍርድ ቤቱ ዳኞች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚገኙ የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት የተከፈቱ ማንኛውም መዝገቦች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

ለ) የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቶች እና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚገኙ የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት የተከፈቱ ማንኛውም መዝገቦች፣ የአስተዳደር መዝገቦች እና ሌሎች መዝገቦች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

## 29. የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ማዘጋጀት

(1) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያሉ ሁሉም የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች በግልጽ ተለይተው በየስራ ዘርፋቸው ይመደባሉ፣

(2) በጉዳይ መዝገብ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የጽሁፍ እና ፎቶ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ በየገጹ ላይ ከአንድ ጀምሮ ተከታታይ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡

(3) የኤግዚቢቶች ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ኤግዚቢቱን በሁሉም በሚታዩት ገጾቹ በኩል በኤሌክትሮኒክ ፎቶግራፍ እና በቪዲዮ በመቅረጽ ይቀመጣሉ፡፡

(4) በፍርድ ቤቶች ውስጥ ስካን (scan) ተደርገው በኤሌክትሮኒክ ሪከርድነት የሚዘጋጁ ሰነዶች ይዘት በትክክል ስካን (scan) መደረጉ በሚመለከተው የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ኦፊሰር ከተረጋገጠ በኋላ በኦፊሰሩ ኤሌክትሮኒክ ፊርማ ተፈርሞ በሚመለከተው መዝገብ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

(5) የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ኦፊሰር የሚከተሉትን መፈፀም አለበት፤

ሀ) ስካን (scan) የተደረገው ሰነድ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ትክክለኛ እና የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ለ) ኤሌክትሮኒክ ሪከርዱን በስርዓቱ ውስጥ ካለው ትክክለኛው የመዝገብ ቁጥር ጋር ያያይዛል፣

ሐ) ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶችን በመዝገባቸው ውስጥ በጊዜው ፋይል ያደርጋል፣

መ) ለኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ተገቢውን የሪከርድ አስተዳደር ሜታዳታ (metadata) ወደ ኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አስተዳደር ስርዓቱ ያስገባል፣

ሠ) በስራ ኃላፊው ሲታዘዝ ወደ ኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አስተዳደር ስርዓቱ በገባው መረጃ ላይ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

(6) በፍርድ ቤቱ ሁሉም ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች በተገቢው ሁኔታ በተደራጀ የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች አስተዳደር ስርዓት ይመራሉ፡፡

## 30. የዳኝነት ጉዳይ ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች አሰያየም

1. የእያንዳንዱ ኤሌክትሮኒክ የጉዳይ መዝገብ ስም በስርዓቱ ውስጥ ለመዝገቡ የተሰጠው ቁጥር ይሆናል፡፡

2. በኤሌክትሮኒክ የጉዳይ መዝገብ ውስጥ ላለ እያንዳንዱ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ የሚሰጠው ስም የመዝገቡ ቁጥር፣ በተከታይነት ወደጎን ሰረዝ (hyphen)፣ እና ለእያንዳንዱ ሪከርድ ካለፈው የሚቀጥለውን ተከታይ ቁጥር በመስጠት ነው፡፡

3. በአንድ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ውስጥ ከአንድ በላይ ገጽ ሲኖር ለእያንዳንዱ ገጽ መለያ ከ 1 ጀምሮ ተከታታይ ቁጥር በገጹ ራስጌ ላይ በጉልህ ይታተምበታል፡፡

31. **የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ማጠራቀሚያ (storage)**

(1) የሁሉም በመታየት ላይ ያሉ የጉዳይ መዝገቦች የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች ከስርዓቱ ጋር በቀጥታ በተገናኘ (online) የሪከርድ ማጠራቀሚያ ስርዓት ውስጥ እንዲጠራቀሙ ይደረጋል፡፡

(2) የተዘጉ የጉዳይ መዝገቦች የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች ከስርዓቱ ጋር በቀጥታ ባልተገናኘ (offline) የሪከርድ ማጠራቀሚያ ስርዓት ውስጥ እንዲጠራቀሙ ይደረጋል፡፡

(3) ፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ወደፊት በቀላሉ መነበብ እንዲችሉ መልካም አቋማቸው በየጊዜው የሚገመገምበትን እና ወደ አዲስ የሪኮርድ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ስርዓት እና የማጠራቀሚያ ቴክኖሎጂ የሚሸጋገሩበትን አሰራር በስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

(4) ወደ አዲስ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አስተዳደር ስርዓት እና የማጠራቀሚያ ቴክኖሎጂ ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ ሁሉም የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች፣ አዲሱ የሪከርድ አስተዳደር ስርዓት እና የማጠራቀሚያ ቴክኖሎጂ ሊያነበው ወደሚችለው የይዘት ቴክኖሎጂ (ፎርማት) እንዲለወጡ ይደረጋል፡፡

32. **የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች አስተማማኝነት እና ደህንነት**

(1) የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶቻቸው ላይ ያልተፈቀደ ለውጥ፣ ስረዛ፣ እና የማስወገድ ተግባር እንዳይከወን፣ ፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች የሚቀመጡበትን የኢንፎርሜሽን ስርዓት ደህንነትን በመጠበቅ እና ሪከርዶቹን የማግኘት (access) ገደብ በማድረግ የሪከርዶቹ አስተማማኝነት እና ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ ይህን ለማስፈጸም ፍርድ ቤቱ በስርዓቱ ተጠቃሚዎች የስራ ድርሻ፣ በተጠቃሚዎች ወደ ስርዓቱ መግቢያ መለያ፣ በጠንካራ የይለፍ ቃል አጠባበቅ፣ እና የባለብዙ መስፈርት መግቢያ (multifactor authentication) አጠቃቀምን በስራ ላይ በማዋል የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ አስተዳደር ስርዓቱ የሚጠቀክበትን ኔትወርክ፣ ማጠራቀሚያ፣ ሰርቨር፣ እና የመተግበሪያ ሶፍትዌር አስተማማኝነት እና ደህንነት እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

(2) ፍርድ ቤቶች የማንነት ማረጋገጫ ወይም ኤሌክትሮኒክ ፊርማ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ምንጭ (origin) እና አስተማማኝነትን ያረጋግጣሉ፡፡ ለዚህም ሲባል፣ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች ወደ ፍርድ ቤቶች ሲላኩም ይሁን ከፍርድ ቤቶች ወደ ሌሎች አካላት ሲላኩ አስተማማኝነታቸው እና ምስጢራዊነታቸው እንዲጠበቅ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች፣ ቴክኖሎጂው በሚገኝበት ቦታ፣ በይፋዊ ቁልፍ መሰረተ-ልማት (public key infrastructure or PKI) ላይ የተመሰረተ የምስጠራ (encryption)



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

አገልግሎቶችን ይተገብራሉ። ከዚህም በተጨማሪ የስርዓቱ ተጠቃሚዎችን ለመለየት፣ ማንነታቸውን ለማረጋገጥ እና ስርዓቱ ውስጥ የመግቢያ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል የግለሰቦች መለያ ስርዓት (identity management system) ይተገብራሉ።

(3) ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶቻቸውን ለማየት፣ ለመሰረዝ፣ ወይም ለማጥፋት የተደረገ ሙከራን የሚመዘግቡበት የኤሌክትሮኒክ ዱካ ኦዲት (audit trail) የሚመዘግቡበት ስርዓትን ይተገብራሉ፤ ይህንንም በመጠቀም የደህንነት መመሪያዎች መተግበራቸውን እና በኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶች ላይ ያልተፈቀደ ተግባር መፈጸሙን ወይም ለመፈጸም ሙከራ መደረጉን ያጣራሉ።

(4) በዝግ ችሎት የሚታዩ ጉዳዮች መዝገብ ውስጥ ያሉ ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች በምስጢር ይያዛሉ፣ ለተፈቀደላቸው የሪከርዱ ተጠቃሚዎች ብቻ ተደራሽ ይሆናሉ።

(5) አሌክትሮኒክ ሪከርዶች ከድንገተኛ ወይም ታስቦበት ከተፈጸመ ጉዳት ወይም ጥፋት እና ከማንኛውም ለውጥ ይጠብቃሉ።

(6) በፍርድ ቤቱ ውስጥ ስካን በማድረግ ወደ ኤሌክትሮኒክ ሪከርድነት የተለወጠ ማንኛውም ሪከርድ ያለው ይዘት አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በሚመለከተው የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ኦፊሰር ኤሌክትሮኒክ ፊርማ ይረጋገጣል።

(7) በፍርድ ቤቱ በኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት አማካኝነት የቀረበ የጉዳይ ሪከርድ በስርዓቱ አማካኝነት ሪከርዱን ባቀረበው ተከራካሪ ወገን ኤሌክትሮኒክ ፊርማ የተረጋገጠ ይሆናል።

(8) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ማንኛውም መጥሪያ፣ ማስታወቂያ፣ ትእዛዝ፣ ውሳኔ፣ ብይን፣ ፍርድ፣ ማዘዣ፣ የምስክር ወረቀት፣ የጥሪ ወረቀት፣ ወይም ማናቸውም ሰነድ መዝገቡን የያዘው ዳኛ ወይም እርሱ ያዘዘው ሬጅስትራር ኤሌክትሮኒክ ፊርማ ትክክለኛነቱ የሚረጋገጥ ይሆናል።

(9) ፍርድ ቤቱ በመደበኛ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሁሉንም በመታየት ላይ ያሉ መዝገቦች ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ቅጂ (ባክአፕ) ይይዛል፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጣል።

(10) ፍርድ ቤቱ ኤሌክትሮኒክ ሪከርድ የተቀመጠባቸው ህንጻዎች፣ ክፍሎች፣ እና መሳሪያዎች ላይ የሚኖር በአካል የሚኖር ተደራሽነትን ይቆጣጠራሉ። ለዚህም ሲባል ፍርድ ቤቱ ወደ ፍርድ ቤቶች ዳታ ሴንተሮች እና ሰርቨር ክፍሎች የሚኖር የአካል ተደራሽነትን ለተፈቀደላቸው ሰዎች በተዘጋጀ መታወቂያ ካርድ፣ በበር ቁልፎች፣ በኤሌክትሮኒክ ቁልፎች ወደ ክፍሎቹ የሚገቡ ሰዎች መመዝገቢያ በማዘጋጀት እና በማስሞላት፣ እና በደህንነት ካሜራዎች ይቆጣጠራሉ።

(11) በፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት የሚታዩ ወይም እንዳይታዩ ታሽገው እንዲቀመጡ የተወሰነባቸው ሪከርዶች በግልጽ ችሎት ከሚታዩ ሪከርዶች ተለይተው ይቀመጣሉ። እነኚህ ሪከርዶችን ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነው የተደራሽነት መቆጣጠሪያ (access control) በተግባር ላይ ይውላል። መዝገቡን የሚመለከተው ዳኛ ብቻ ሪከርዱ እንዳይታይ ታሽጎ እንዲቀመጥም ሆነ ለእይታ ክፍት እንዲሆን መወሰን ይችላል።

(12) ፍርድ ቤቶች ምስጢራዊ መረጃ ወደያዙ ሪከርዶች እና እንዳይታዩ ወደታሸጉ ሪከርዶች የሚደረጉ ተደራሽነቶችን የሚቆጣጠሩበት የቴክኖሎጂ ስርዓት ይተገብራሉ፡፡ ለዚህም ሲባል ፍርድ ቤቶች ሪኮርዶችን የመመስጠር (encryption)፣ የማሸግ (sealing)፣ እና ከሪከርዶች ውስጥ ሚስጢር የያዙ የተወሰኑ የሪከርድ ክፍልን በጥቁር ቀለም የመሸፈን (redaction) ቴክኖሎጂዎችን ይተገብራሉ፡፡

(13) ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ የጉዳይ መዝገቦችን በፍርድ ቤቶቹ ውስጥ ለህዝብ ክፍት ሲያደርጉ መዝገቦቹ ተደራሽ የሚሆኑባቸው በፍርድ ቤቶቹ ለህዝብ ክፍት ሆነው የሚተከሉ ኮምፒውተሮች ላይ ጠንካራ የደህንነት ውቅር ማለትም ውስን የኔትወርክ ተደራሽነት፣ ከማዕከል የሚደረግ የስርዓት አስተዳደር እና ቁጥጥር፣ እና እነኚህ ኮምፒውተሮች ከሌሎች የፍርድ ቤቶች የውስጥ አገልግሎት ኮምፒውተሮች ለይቶ የማስተዳደር አሰራር ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

(14) ፍርድ ቤቶች ኤሌክትሮኒክ ሪከርዶቻቸውን ከጠላፊዎች (hackers) ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ የኔትወርክ ደህንነት ስርዓቶችን ይተገብራሉ፡፡

(15) ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶቻቸውን አቋም (status) ለህዝብ ክፍት ከሆነ ወደ ዝግ ወይም ከዝግ ወደ ክፍት የሚለወጡበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋሉ፡፡

## 33. ለኤሌክትሮኒክ የፍርድ ቤት ሪኮርድ የሚኖር ተደራሽነት

(1) በዝግ ችሎት ከሚታዩ ጉዳዮች በስተቀር፣ ፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ የዳኝነት ስራ ሪከርዶች ውስጥ የግለሰብ መለያዎች በመዝገቡ ውስጥ ካሉ ሁሉም አቤቱታዎች እና ኤግዚቢቶች ላይ እንዳይታዩ አድርጎ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በጥቁር ቀለም በመሰረዝ (redaction) መዝገቦቹ ለህዝብ ክፍት ይደረጋሉ፡፡ የሚከተሉት መረጃዎች ከመዝገቦች ውስጥ ካሉ ሁሉም ሪከርዶች እንዳይታዩ አድርጎ በጥቁር ቀለም ይሰረዛል፤

(ሀ) ከ 18 ዓመት እድሜ በታች የሆኑ ልጆች ስሞች፣
(ለ) የግለሰብ የትውልድ ቀን፣
(ሐ) የባንክ ሂሳብ ቁጥር (ከመጨረሻ አራት አሃዝ በስተቀር) ፣
(መ) የግለሰብ የፋይናንስ መረጃ፣
(ሠ) የብሔራዊ መታወቂያ (ፋይዳ) ቁጥር (ከመጨረሻ አራት አሃዝ በስተቀር) ፣
(ረ) ማንኛውም የግለሰብ መለያ፣ የመንጃ ፈቃድን ጨምሮ
(ሰ) የህክምና መረጃዎች፣
(ሸ) የስራ ቅጥር መረጃዎች፣
(ቀ) የባለቤትነት ወይም ምስጢራዊ የንግድ መረጃ፣
(በ) የእስር ትእዛዝ፣
(ተ) የብርበራ ትእዛዝ፣
(ቸ) የተጎጂ መረጃ፣
(ኀ) የምስክር መረጃ፣
(ነ) ብሄር፣
(ኘ) እድሜ፣

(ኣ) በሌላ ህግ ጥበቃ የተደረገለት ማንኛውም የግለሰብ መረጃ።

(2) በዝግ ችሎት እንዲታዩ እንዲሁም ከህዝብ ተደራሽነት ውጪ እንዲሆኑ በዳኛ ውሳኔ የተሰጠባቸው የፍርድ ቤት ሪከርዶች ለህዝብ ተደራሽነት ክፍት አይደረጉም።

(3) ፍርድ ቤቱ ህግን በጠበቀ ሁኔታ የፍርድ ቤቶቹ የኤሌክትሮኒክ የጉዳይ መዝገቦች በፍርድ ቤቶች ውስጥ እና በድረ-ገጽ አማካኝነት ለህዝብ ክፍት እንዲሆኑ ያደርጋል።

## 34. <u>የሪኮርድ ቆይታ ጊዜ እና ጥበቃ</u>

(1) ማንኛውም የወረቀትም ሆነ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ በህግ ለተደነገገው ጊዜ ብቻ በፍርድ ቤት እንዲቀመጡ ይደረጋል።

(2) የማንኛውም የወረቀት ሪኮርድ (ማስረጃን ጨምሮ) በፍርድ ቤት የሚኖረው የቆይታ ጊዜው ሲጠናቀቅ፣ ለወደፊት ጥበቃ፣ ሪኮርዱ ወደ ብሔራዊ መዛግብት እና ላይብራሪ ኤጀንሲ ለወደፊት ጥበቃ ይተላለፋል።

(3) የወረቀትም ሆነ የኤሌክትሮኒክ ሪኮርዶችን ወደ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብት እና ላይብራሪ ኤጀንሲ ከማስተላለፋቸው በፊት፣ የግለሰብ እና የሙያ ምስጢርን ለመጠበቅ፣ ፍርድ ቤቱ ማንኛውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ።

## 35. የተጠቀሚዎች የወል ግዴታዎች

(1) ማንኛውንም ሰነድ በስርዓቱ አማካኝነት ከማቅረቡ በፊት የሰነዱ አቅራቢ የሆነው ተከራካሪ ሰነዱ ከቫይረስ እና ማልዌር ነጻ መሆኑን ከጊዜው ጋር በተጣጣመ ፀረ-ቫይረስ ሶፍትዌር ስካን (scan) አድርጎ ከቫይረስ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

(2) ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ ከአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓቱ ጋር ተቀናጅቶ በተተገበረ ፀረ-ቫይረስ ሶፍትዌር ሰነዶች ከቫይረስ እና ማልዌር ነጻ ስመለሆናቸው ስካን (scan) ይደረጋል። ቫይረስ እና ማልዌር ስለመኖሩ በፀረ-ቫይረስ ሶፍትዌሩ ከተረጋገጠ፣ ሰነዱ ከቫይረስ ወይም ማልዌር ነጻ እስኪሆን ድረስ ወደ ስርዓቱ የሰነድ ማጠራቀሚያ አይተላለፍም።

## 36. ተቋማዊ ግዴታዎች

(1) ፍርድ ቤቱ በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓቱ አማካኝነት ያልተቆራረጠ አገልግሎት እንዲሰጥ እና በስርዓቱ ላይ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ጉዳቶች ቢደርስ በስርዓቱ በኩል የሚሰጡት አገልግሎት ሳይቋረጥ መስጠት እንዲቻል ያልቋረጠ አገልግሎት አሰጣጥ እና ከጉዳት የማገገም እቅድ እና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በማዘጋጀት በተሟላ ሁኔታ እንዲካተቱ ያደርጋሉ፤

(2) ፍርድ ቤቱ ያልተቋረጠ አገልግሎት አሰጣጥ እና ከጉዳት የማገገም ፕላን፣ ስርዓቱ በሁሉም ቀናቶች ሙሉ ቀን ያልተቋረጠ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያካትታል።

(3) በተሟላ ሁኔታ በድረ-ገጽ መልክ የለማ የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ሶፍትዌር ከፍርድ ቤቱ የተቀናጀ የጉዳዮች አስተዳደር የመረጃ ስርዓት ሶፍትዌር፣ የአስተዳደር እና ፋይናንስ ስርዓት ሶፍትዌር፣ እና የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ አስተዳደር ስርዓት ሶፍትዌር ጋር በተሟላ ሁኔታ ተቀናጅቶ እንዲሰራ ይደረጋል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

37. **በአቤቱታ አቀራረብ የቀረቡ ሰነዶች የወረቀት ኮፒን ስለማቅረብ፣**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየጊዜው በሚያወጣቸው ሰርኩላሮች አማካኝነት ለአቤቱታዎች የወረቀት ኮፒ የሚቀርብባቸውን እና በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ የማይቀርብባቸውን የጉዳይ ዓይነቶች ዝርዝርን ሊያወጣ ይችላል።

38. ስለ ውክልና

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር በዚህ መመሪያ የተሰጡትን ኃላፊነት እና ተግባራት እንደ አስፈላጊነቱ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

39. **የስርዓቱ ድረ-ገጽ አጠቃቀም መምሪያ**

(1) ፍርድ ቤቱ የስርዓቱ ድረ-ገጽ አጠቃቀም ደንብና ሁኔታዎችን፣ የአጠቃቀም መምሪያ፣ እና የድረ ገጹ አጠቃቀም የቪዲዮ አጋዥ ስልጠና (Tutorial) በማዘጋጀት በስርዓቱ ድረ-ገጽ ላይ ይለጥፋል።

(2) ተከራካሪዎች የስርዓቱ ድረ-ገጽ አጠቃቀም ደንብና ሁኔታዎችን፣ የአጠቃቀም መምሪያ፣ እና የድረ ገጹ አጠቃቀም ዙሪያ በፍርድ ቤቱ የሚዘጋጀውን አጋዥ ስልጠና (Tutorial) በአግባቡ መከታተል፣ መጠቀም እና መፈፀም አለባቸው።

40. **አስገዳጅ ሁኔታዎች**

(1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስገዳጅነቱ እንዲቀር ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር፣ ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ በጠበቆች እና ዓቃቢያነ ህጎች የተወከሉ የፍትሃብሔር እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ሰርኩላር ላይ የሚገለፁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማንኛውንም አቤቱታዎች ወይም ማንኛውንም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚቀርብ ሰነድ በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት አማካኝነት መቅረብ አለበት።

(2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየጊዜው በሚያወጣቸው ሰርኩላሮች አማካኝነት አቤቱታ አቀራረብን በግዴታ ከመጠቀም ነጻ የሚሆኑ ተከራካሪ ወገኖች፣ የተከራካሪ ወገን ዓይነቶች እና የጉዳይ ዓይነቶች ዝርዝርን ይወስናል።

(3) የፍርድ ሂደቶችን በተመለከተ በዝግ ችሎት ከሚታዩ ጉዳዮች እና በሚስጢር ከሚጠበቁ ሰነዶች እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየጊዜው በሚያወጣቸው ሰርኩላሮች ላይ በሚገለጹ አቤቱታ አቀራረብን በግዴታ ከመጠቀም ነጻ ከሚሆኑ ተከራካሪ ወገኖች፣ የተከራካሪ ወገን ዓይነቶች፣ እና የጉዳይ ዓይነቶች በስተቀር፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማናቸው ሰነዶች በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት አማካኝነት መቅረብ አለባቸው።

41. <u>ስለ ቅጣት እና መመሪያውን ያለማክበር ስለሚስከትለው ውጤት</u>

(1) በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ክልከላዎችን በመተላለፍ የኤሌክትሮኒክ ሠነዶችን ወይም የርቀት መስማት ቅጂዎችን አላግባብ የተጠቀመ ወይም ያሰራጨ ሰው በችሎት መድፈር ሊቀጣ ይችላል።

(2) በአሌክትሮኒክ ዘዴ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ሠነድ የዋናው ሰነድ ትክክለኛ ቅጂ መሆን አለበት። ለፍርድ ቤት በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚቀርብ ሠነድ ሃሰተኛ ሆኖ ከተገኘ ሠነዱን ያላከው ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

(3) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሰነድ ሲቀርብ፤ ክርክር ሲመራ ወይም በርቀት መስማት ወቅት የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ የማያከብር ወገን ካለ ችሎቱ ትዕዛዝ ያላከበረውን ወገን አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ ሊቀጣው ይችላል።

(4) በተለያዩ ፋይሎች የተያዙ ጉዳዮች ሰነዶች ተደባልቀው በአንድ ላይ በአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓቱ በኩል ከተላኩ ሰነዶቹ በሙሉ ውድቅ ይደረጋሉ።

(5) ይህንን መሪያ እና ተያያዥ ሌሎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጡ መመሪያዎችን በተቃረነ ሁኔታ በስርዓቱ በኩል ሰነዶች የቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሰነዶቹን ውድቅ ሊያደርጋቸው ይችላል።

42. <u>የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ኤሌክትሮኒካዊ የይዘት ውቅር (ፎርማት) እና የይዘት መጠን</u>

(1) የአሌክትሮኒክ ሪከርድ ኤሌክትሮኒካዊ የይዘት ውቅር (ፎርማት) በዚህ መመሪያ አባሪ 6 ስር በተመለከተው አግባብ መሆን አለበት።

(2) የማንኛውም በስርዓቱ አማካኝነት የሚቀርብ ሰነድ የይዘት መጠን በዚህ መመሪያ አባሪ 7 ላይ በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

43. <u>የቴክኒክ ችግሮች</u>

(1) በቴክኒክ ችግር ምክንያት በስርዓቱ አማካኝነት ሰነዶችን ለማቅረብ ያልቻለ ሰው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መደበኛ የስራ ሰዓት ከሆነ የፍርድ ቤቱ በሚያዘጋጀው ከክፍያ ነፃ የጥሪ ማዕከል የስልክ መስመር ላይ ደውሎ የገጠመውን የቴክኒክ ችግር በቃል በማስረዳት፣ ወይም በማንኛውም ጊዜ ለኢሜይል አድራሻ support@FSCc.gov.et የገጠመውን የቴክኒክ ችግር ዘርዝሮ በጽሁፍ በመላክ አፋጣኝ የቴክኒክ ድጋፍ ማግኘት ይችላል።

(2) በስርዓቱ በኩል የተላከ ሰነድ በስርዓቱ የቴክኒክ ችግር ምክንያት በጊዜው ካልደረሰ፣ የተፈቀደለት ተጠቃሚ ማስረጃውን ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ ሰነዱ በጊዜው ባለመድረሱ ምክንያት ከመጣበት ግዴታ ወይም የመብት ማጣት ነጻ እንዲሆን መጠየቅ ይችላል።

44. **የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ስለማልማት**

አንድ የቴክኖሎጂ ውጤት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በውስጥ አቅም ለምቶ ወደ ስራ እንዲገባ ከመደረጉ በፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚቋቋም የባለሙያዎች ቡድን ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

45. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

(1) እስካሁን አገልግሎት የሚሰጠባቸው በቴክኖሎጂ የተደገፉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራት እና ፍርድ ቤቱ አሁን ባለው መሠረተ ልማት መተግበር የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት በተቀናጀ የጉዳዮች አስተዳደር የመረጃ ስርዓት (Integrated Case Management Information System) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ደረጃ በደረጃ የሚተገበረው አስፈላጊ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መኖሩ በፍርድ ቤቱ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኃላፊ ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ማናቸውም የሰበር እና የይግባኝ ማመልከቻ፣ ለነዚህ የሚቀርቡ መልሶች፣ የመልስ መልሶች እና በአባሪነት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ከጽሑፍ ቅጂ በተጨማሪ የኮምፒዩተር ቅጂ ሠነድም አብሮ መያያዝ አለበት::

(4) ተገልጋዮች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ ቤት እና ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህን አንጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፁ የኮምፒዩተር ቅጂ ሠነዶችን እንዲያቀርቡ የሚደረገው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው ማስታወቂያ ለህዝብ ሲገለፅ ነው፡፡

(5) የኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቤቱታ አቀራረብ፣ ሙግት ማከናወን ስርዓት አስፈላጊ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ተሟልቶ ሙሉ በሙሉ እስከሚተገበር ድረስ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ወይም የሰበር ማመልከቻ ማቅረብ የሚፈልግ ወገን የመዝገቡ ግልባጭ የኮምፒዩተር ቅጂ በኤሌልትሮኒክ ዘዴ ወደ ሰበር ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እንዲላክለት ማመልከት አለበት፡፡

(6) የመዝገብ ግልባጭ በኮምፒዩተር ቅጂ እንዲልክ ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተቻለ ፍጥነት መዝገቡን በአሌክትሮኒክ ዘዴ ወደ ሰበር ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መላክ አለበት፡፡

(7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተጠቀሰው ቢኖርም ባለጉዳይ የውሳኔ ግልባጭ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለሰበር ወይም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲላክ ጥያቄ መቅረቡ ወይም የይግባኝ ሰነዱ ግልባጭ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወደ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መላኩ የይግባኝ ቅሬታ እንደቀረበ አይቆጠርም፡፡

(8) የኮምፒዩተር ቅጂው የተላከለት ፍርድ ቤትም ሠነዱን በፎልደር በማስቀመጥ የይግባኝ ማመልከቻ በቀረበበት ጊዜ አባሪ በማድረግ የመዝገቡ አካል እንዲሆን ያደርጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

46. <u>መመሪያው የሚሻሻልበት ሁኔታ</u>

(1) የፍርድ ቤቱን አሰራር በተመለከተ የሚወጡ መመሪያዎችን፣ የቴክኖሎጂ እድገትን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ ይህ መመሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊሻሻል ይችላል።

(2) በዚህ መመሪያ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማሻሻያዎች በጊዜው በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንዲደርሳቸው እና እንዲያውቁት ይደረጋል።

47. <u>የመመሪያው ተፈጻሚነት የሚጀምርበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመስከረም 23 ቀን 2018 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሃሴ 23 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## አባሪ 1

**ተቋማዊ ተከራካሪ ለመሆን የሚቀርብ ማመልከቻ (ለጥብቅና አገልግሎት ድርጅት)**

**የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱ ስም፡ ........................................................**

የድርጅቱ አድራሻ፡- ክልል..........................ከተማ..................................ክፍለ ከተማ................................ ወረዳ.........................የቤት ቁጥር.............

የቢሮ ስልክ ቁጥር፣............................... ፖ.ሳ.ቁ. ..................የኢሜይል አድራሻ......................................................

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስም፣.............................................................. አድራሻ፣ ክልል................. ከተማ........................ክፍለ ከተማ.....................ወረዳ.................. የቤት ቁጥር.............

የሞባይል ስልክ ቁጥር፣...............................ፖ.ሳ.ቁ. ............የኢሜይል አድራሻ........................................................

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አገልግሎት ለመስጠት የድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ ቁጥር .....................

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የድርጅቱ የጥብቅና ፈቃድ አይነት .........................................

ከላይ ስሙ እና ሌሎች መረጃዎቹ በዝርዝር የተመለከተው የህግ ቢሮ ፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ተጠቃሚ ሆኖ እንዲመዘብልን እና በቢሮው ስር የሚሰሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አገልግሎት የሚሰጡ የሚከተሉት ጠበቆች የስርዓቱ ተጠቃሚነት ፈቃድ እንዲሰጥልን እናመለክታለን፡፡

| ተ.ቁ. | የጠበቃው/ረዳቱ ስም | የጥብቅና ፈቃድ ቁጥር | የጥብቅና ፈቃድ አይነት | የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር | ሞባይል ስልክ ቁጥር | የኢሜይል አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

የህግ ቢሮው ዋና ሥራ አስኪያጅ ስም፣ ..........................................................................................

ፊርማ.......................................... ቀን ..................................................

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እስ/ መዝገብ ቤት
Federal Supreme Court The Federal Democratic Republic of Ethiopia

## አባሪ 2

## ግለሰብ ተከራካሪ ለመሆን የሚቀርብ ማመልከቻ (ለጠበቆች)

**በጥብቅና ፈቃዱ ላይ የሰፈረው የጠበቃው መጠሪያ ስም፣ ..........................................**

የጠበቃው ቢሮ አድራሻ፣ ክልል.........................................ከተማ..................................ክፍለ ከተማ......................... ወረዳ.........................የቤት ቁጥር.............

የቢሮ ስልክ ቁጥር፣.................................... የሞባይል ስልክ ቁጥር፣..................................ፖ.ሳ.ቁ. ........................... የኢሜይል አድራሻ....................................................

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አገልግሎት ለመስጠት የጥብቅና ፈቃድ ቁጥር ...

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ አይነት ................................................

የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ..........................................

ከላይ ስሜ እና ሌሎች መረጃዎቼ በዝርዝር የተመለከተው ጠበቃ ፍርድ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ስርዓት ተጠቃሚ ሆኜ እንድመዘገብ እና የስርዓቱ ተጠቃሚነት ፈቃድ እንደሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

በጥብቅና ፈቃዱ ላይ የሰፈረው የጠበቃው መጠሪያ፣ ................................
የጠበቃው ሙሉ ስም፣ ...........................................................
ፊርማ................................................................ ቀን ..............

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስ/ መዝገብ ቤት
The Federal Supreme Court Federal Democratic Republic of Ethiopia

## አባሪ 3

## ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ሰነዶች ዝርዝር

### ለጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች

(1) የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱ ፈቃድ፣

(2) በስሩ የሚሰሩ ጠበቆች የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ፣

(3) በስሩ የሚሰሩ ጠበቆች የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

### ለጠበቆች

(1) የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ፣

(2) የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣

## አባሪ አራት

## ስለ አቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓት የድረ-ገጽ አድራሻዎች

1. የአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓትድረ ገጽ አድራሻ https://fc.ecourt.gov.et ነው።
2. ጠበቆች ምዝገባ የሚያከናውኑበት የድረ ገጹ አድራሻ https://fc.ecourt.gov.et/registerነው።
3. የአቤቱታ አቀራረብ እና ሙግት ማከናወን ስርዓትን ለመጠቀም የሚገባበት የድረ ገጹ አድራሻ https://fc.ecourt.gov.et/login ነው።

## አባሪ አምስት

## የሰነዶች ይዘት አቀራረብ (ፎርማት)

1. በስርዓቱ አማካኝነት የቀረበ ማንኛውም ሰነድ ፍርድ ቤቱ በሚጠይቁት የሰነዶች ይዘት አቀራረብ (ፎርማት) መሰረት መቅረብ ይኖርበታል፡
2. በስርዓቱ አማካኝነት የቀረበ ሰነድ ለጽኁፍ ፍለጋ ዝግጁ በሆነ (searchable) PDF/A ፎርማት የተዘጋጀ ሆኖ በቅርብ ጊዜ በስራ ላይ በዋለ Adobe Reader ሶፍትዌር ሊነበብ በሚችል የሰነድ ይዘት አቀራረብ (ፎርማት) መቅረብ አለበት።
3. ማንኛውም በስካነር ተቀርጾ (Scanned) የሚቀርብ ሰነድ በጥቁር እና ነጭ በ 300 dots per inch (dpi) መዘጋጀት አለበት።
4. ማንኛውም በስካነር ተቀርጾ (Scanned) የተዘጋጀ ሰነድ ለጽሑፍ ፍለጋ ዝግጁ እንዲሆን (searchable) ተደርጎ መዘጋጀት አለበት።

## አባሪ ስድስት

## የሰነዶች ከፍተኛ የይዘት መጠን

1. የማንኛውም በስርዓቱ አማካኝነት የሚቀርብ ሰነድ የይዘት መጠን ከአምስት ሜጋባይት (megabyte) መብለጥ የለበትም።
2. በስርዓቱ አማካኝነት የሚቀርበው ሰነድ የይዘት መጠን ከአምስት ሜጋባይት (megabyte) የሚበልጥ ከሆነ ሰነዱ ከአምስት ሜጋባይት በታች በሆኑ የተለያዩ ክፍሎች ተከፍሎ መቅረብ አለበት። በዚህ ሁኔታ ሰነዱ ተከፋፍሎ በሚላክበት ጊዜ ለሰነዱ ከተሰጠው ስም ቀጥሎ "ክፍል 1"፣ ክፍል 2"፣ ወ.ዘ.ተ. የሚል በማስፈር የሰነዱ ክፍሎች በግልጽ እንዲለዩ መደረግ አለበት፡
3. የአንድ በስርዓቱ አማካኝነት የሚቀርብ አቤቱታ ድምር የይዘት መጠን ከ 30 ሜጋባይት መብለጥ የለበትም።

## አባሪ ስምንት

## የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ይዘት ቅርጽ (ፎርማት)

1. ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሪከርዶች ይዘት ቅርጽ (ፎርማት) በሚመርጠበት ጊዜ፣ የሪከርዱ ይዘት ቅርጽ (ፎርማት) በፍርድ ቤቶች እና አጋር ተቋሞች (ማለትም በጠቅላይ አቃቤ ህግ፣ ፌዴራል ፖሊስ እና ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች)፣ እንዲሁም በተጠቃሚው ህዝብ ዘንድ አሁን እና ወደፊት ሊኖሩ ይችላሉ ከሚገመቱ ቴክኖሎጂዎች ጋር የሚኖረው

ተናባቢነትን፣ እና በመስኩ ያለውን አለም አቀፍ ስታንዳርድ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

2. ጽሁፍ ወይም ፎቶ ስካን (scan) በማድረግ ወይም ከኢንፎርሜሽን ስርዓት በቀጥታ በማውጣት (ለምሳሌ ከጉዳይ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ስርዓት) የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ ሊዘጋጅ ይችላል። በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀ የጽሁፍ ወይም ፎቶ የኤሌክትሮኒክ ሪከርድ በ PDF/A የይዘት ቅርጽ (ፎርማት) ይቀመጣል።

3. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁሉም የድምጽ ሪከርዶች በኤሌክትሮኒክ የድምጽ ሪከርድ መሳሪያ ተዘጋጅተው በ Wave file (.wav) ወይም MPEG Layer-3 file (.mp3) የይዘት ቅርጽ (ፎርማት) ይቀመጣሉ።

4. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁሉም የቪዲዮ ሪከርዶች በኤሌክትሮኒክ የቪዲዮ ሪከርድ መሳሪያ ተዘጋጅተው በ Audio Video Interleave file (.avi) ወይም Windows Media Video file (.wmv) የይዘት ቅርጽ (ፎርማት) ይቀመጣሉ።

5. ፍርድ ቤቱ የወረቀት ሰነዶችን ስካን (scan) አድርገው ወደ ኤሌክትሮኒክ ሪከርድ በሚለውጡበት ጊዜ፣ ለቅጂው ጥራት ሲባል፣ 300 dots per inch (dpi) ይጠቀማሉ። ከዚህ በተጨማሪ በነጭ ወረቀት ላይ በጥቁር ቀለም ጽሁፍ የተዘጋጀ ሰነድ ግሬይ ስኬል (grayscale) የከለር መምረጫ (color palette) በጥቅም ላይ ይውላል።

6. የቴክኖሎጂ እድገትን ተከትሎ ከላይ የተመለከቱት ሊሻሻሉ ይችላሉ።

# <u>አባሪ 9</u>

## <u>ለኤሊክትሮኒክ ሙግት የፍቃደኝነት መሙያ ፎርም</u>

### <u>ቅጽ 1፡ (ለወንጀል እና ለፍትሐብሔር ጉዳዮች ተፈፃሚ የሚሆን)</u>

1. ስም፡
2. የመለያ ቁጥር (CID)
3. ስልክ ቁጥር
4. የፍርድ ቤቱ ስም

ከሁለቱ አንዱን ይምረጡ

- ○ ምርጫ 1፡ በችሎት ቀርቦ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን
- ○ ምርጫ 2፡ በርቀት ሆኖ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን

ምርጫዎ በርቀት ሆኖ በአሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን ከሆነ የሚከተሉትን አማራጭ አድራሻዎች ይሙሉ

1. ስልክ ቁጥር
2. አማራጭ ስልክ ቁጥር፡
3. የኢ ማይል አድራሻ
4. እኔ ከላይ ስሜ እና አድራሻዬ የተጠቀሰው ተከራካሪ ወገን/ ምስክር ወይም ባለሙያበፍርድ ቤቱ በተዘጋጀው የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሙግት ማረቢያ ዘዴ ሙግት ለማከናወን ወይም ለመመስከር ፍቃደኛ መሆኔን አረጋገጣለሁ።

በዚህ የክርክር አስተዳደር ዘዴ ለፍርድ ቤቱ የማቀርበው ክርክር ወይም የምስጠውን ቃል ሀ) አስገዳጅ መሆኑን እና በማስረጃነት ሊቀርብየሚችል መሆኑን፤

ለ) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረጉ የርቀት ሙግቶችን ሠነዶችን ብቀርፅ፤ በማናቸውም ብዙሃን መገናኛ ባስተላልፍ ወይም ብጠቀም በችሎት መድፈር ወንጀል እንደምጠየቅ በመስማማት

ሐ) ሃሰተኛ ሠነድ በአሌክትሮኒክ ዘዴ ልፍርድ ቤቱ ባቀርብ በማጭበርበር እና በሃሰተኛ ሰነድ በማቅረብ ወንጀል እንደምጠየቅ በመስማማት

መ)በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚደረግ የሙግት ስርዓት ወቅት የማላከብረው ማናቸውም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቢኖር በችሎት መድፈር ተጠያቂ እንደምሆን በፊርማዬ አጋግጣለሁ።

ፊርማ፡

ቀን፡

ለቢሮ አገልግሎት ብቻ የሚውል

1. የተቀባይ ስም
2. ፊርማ እና ማህተም

## ቅጽ 2 ፡ ለተመዘገቡ እና በሂደት ላይ ለሚገኙ አካላት የፍቃደኝነት መሙያ ፎርም

ስለተከራካሪ ወገኖች ዝርዝር መረጃ

1. የከሣሽ/ ዓቃቤ ህግ/ የአመልካች ስም
2. የተከሣሽ/መልስ ሰጪ ስም ስም
3. የተከራካሪ ወገኖች ስልክ፡
4. የፍርድ ቤቱ ስም
5. የጉዳዩ ዓይነት እና የመስገብ ቁጥር
6. ክርክሩ ,ያለበት ደረጃ
7. የተላኩ ሠነዶች

ከሁለቱ አንዱን ይምረጡ

- ○ ምርጫ 1፡ በችሎት ቀርቦ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን
- ○ ምርጫ 2፡ በርቀት ሆኖ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን

ምርጫዎ በርቀት ሆኖ በአሌክትሮኒክ ዘዴ ምዝገባ ማከናወን ከሆነ የሚከተሉትን አማራጭ አድራሻዎች ይሙሉ

5. ስልክ ቁጥር፡
6. አማራጭ ስልክ ቁጥር፡
7. የኢ ማይል አድራሻ
8. እኔ ከላይ ስሜ እና አድራሻዬ የተጠቀሰው ተከራካሪ ወገን/ ምስክር ወይም ባለሙያ በፍርድ ቤቱ በተዘጋጀው የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሙግት ማረቢያ ዘዴ ሙግት ለማከናወን ወይም ለመመስከር ፍቃደኛ መሆኔን አረጋገጣለሁ።

   በዚህ የክርክር አስተዳደር  ዘዴ ለፍርድ ቤቱ የማቀርበው ክርክር ወይም የምስጠውን ቃል ሀ) አስገዳጅ መሆኑን እና በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል መሆኑን፤

   ለ) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረጉ የርቀት ሙግቶችን ሠነዶችን ብቀርፅ፤ በማናቸውም ብዙሃን መገናኛ ባስተላልፍ ወይም ብጠቀም በችሎት መድፈር ወንጀል እንደምጠየቅ በመስማማት

   ሐ) ሃሰተኛ ሠነድ በአሌክትሮኒክ ዘዴ ልፍርድ ቤቱ ባቀርብ አግባብነት ባለው የወንጀል እንደምጠየቅ በመስማማት

   መ) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚደረግ የሙግት ስርዓት ወቅት የማላከብረው ማናቸውም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቢኖር በችሎት መድፈር ተጠያቂ እንደምሆን በፊርማዬ አጋግጣለሁ፡;